# የምሁራን ደናቁርት ፬ (Educated Bums)

አንዳንዱ ሰው ትምህርት በጨመረ ቁጥር አእምሮውም እየሰፋና እየዳበረ እንደመሄድ እየጠበበ የሚሄድበት ሁኔታ ያለ ይመስላል። ይኸም በመሰረቱ ከትምህርቱ ልቀት የተነሳ የዕውቀቱ ጥልቀት በጨመረ ቁጥር የይዞቱ መጥበብ ተያይዞ የሚመጣ ሁኔታ ይሆን? ለዚህም ይሆን ያገራችን ሰዎች 'ከተማረ የተመራመረ' ይበልጣል ይሚሉት?

ዛሬ የምናያቸው ጥቂት ኣጉል ምሁራንም ልዩ-ልዩ ቡድኖችን ፈጥረው፤ 'በኢትዮጵያ ላይ የኢኮኖሚ ጫና እንዲደረግ' የኣሜሪካና የኤውሮጳ ኣገሮችን ሲለምኑ፣ ኢትዮጵያ የተበደረችው ዕዳ እንዳይሰረዝላት፣ ተጨማሪ ብድርም እንድትከለከል፣ "ማንኛቸውም እርዳታም ኣትሰጧት!" እያሉ ሲዘላብዱ ስናይ፣ "ወይ ዕብደት!" እያልን እናዝናለን።

ዕብደታቸውን ለመግለጽ ትንሽ ማስረጃ ለማቅረብ ያህል፦ "My Fashion" በተባለው መጽሔት ከማስታወቂያ ገጽ ላይ ያየሁት፣ "Trust ሕይወት" የተባለ ኮንዶም ኣራቱን በኢትዮጵያ ሃምሳ ሳንቲም እንደሚገኙ ይነግራል። የኣንዱ ኮንዶም ዋጋ በኣሜሪካ ኣንድ ሳንቲም ተኩል ሲሆን፣ ይህ በኣሜሪካ ለድሆች ነፃ ኮንዶምና የድራግ መርፌ የሚሰጡ ድርጅቶች እንኳን ከሚገዙበት (wholesale price) በታች ዝቅ ያለ ዋጋ ሆኖ ኣግኝተነዋል። ታድያ ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው።

ይህ ሊሆን የቻለው ኢትዮጵያ እርዳታ በማግኘትዋ ኣይደለም ወይ? እነዚህ የምሁራን ደናቁርት ግን እርዳታ ኣትስጡ ሲሉ ሕዝባቸውን ለኤይድስ በሽታና ሞት ኣሳልፈው እንደዳረጉት ያውቁታል? በጣም ያጠራጥረናል! ቢያውቁትም ባያውቁትም ሕዝቡን ለኤይድስ ሕመምና ሞት የሚዳርግ ሰው ከሓዲ ለመሆኑ ምን የሚያጠራጥር ኣለ?

ከኣሜሪካ ከራድዮ ጣብያዎች ትውውቅ ያለው ወዳጄ፤ "ከፈለግኸ ላገናኝህና በሬድዮ ግጠማቸው?" ቢለኝ፤ "ከዕብዶች ጋር ምን ግጥሚያና ኣፍ መካፈት ያስፈልጋል? ከሓዲዎችን ምራቄ ጺቅ ብየ ከማለፍ ሌላ፣ ሰው ብሎ ማነጋገር ራሴን ማዋረድ ነው!" ኣልኩት። ሰዉ እንዲጠየፋቸውና እንዲያገልላቸው ይገባል ያልነውም ለዚህ ነው።

የጦር ሚኒስተር የነበሩት ሃገር ወዳዱና ጀግናው ራስ ሙሉጌታ፣ ማይጨው በዘመቱ ጊዜ፣ ኣሌኻንድሮ ዴልባዬ የተባለው ኩባዊ ኢትዮጵያን ለመርዳት መጥቶ ከጎናቸው ቆሞ ሲዋጋ፣ ጦርነቱ ጋብ ብሎ ጣልያኖቹ መንገድ ሲከፍቱ፣ ድልድይ ሲሠሩ አይቶ፣ ሊመክራቸው፣ ጠላት በዚህ መንገድ ታንክና ከባድ የሆነ የጦር መሣሪያ ሊያመጣብን ነውና፤ "የሚሠሩት ሥራ ላይ ጥቃት እንሰንዝር" ኣላቸው።

ሲመልሱለትም፤ "እነኚህ የመኪና መንገዶች ለኣቢሲንያ ጠቃሚ ይሆናሉ። ጣልያኖች ይሠሯቸዋል፣ እኛ ደግሞ እንገለገልበታለን።" በድጋሚም መንገዶቹን ለማፍረስ የግድ ሲላቸው፤ "በዚህ በኩል ምንም ስጋት ኣይግባብህ… እኛ ራሳችንም ብንሆን እነርሱን ለማጥቃት መንገድ ያስፈልገናል። ጣልያን እንዲሠራው መተው ኣለብን። ለሠራዊታችን መገልገያ ይሆናል። የኢትዮጵያም ሃብት ሆኖ ይቀራል።"

ራስ ሙሉጌታ ከሃገር የቄስ ትምህርት ሌላ ለፕሮፌሰርነት ቀርቶ የአንደኛ ደረጃም ትምህርት መማራቸውን እንጃ፣ ግን ምን ያህል አስተዋይና አርቀው የማየት ችሎታ እንደ ነበራቸው ዛሬ በግልጽ እናያለን። ከተማረ የተመራመረ የሚባልም ለዚህ ነው።



- መቀሌ ላይ በተደረገው ውጊያ ህይወታቸው ያለፈው የኢትዮጵያ ጦር ሚኒስትር ራስ ሙሉጌታ

ራስ ሙሉጌታ በጦር ግንባር ሕይወታቸውን ለሃገራቸው ሰዉ። ጣልያንም ኢትዮጵያን ለአጭር ጊዜ ወርሮ ያዘ። ራስ የተናገሩት የትንቢት ቃል ደርሶ፣ እንዳሉት መንገዶቹ የኢትዮጵያ ሃብት ሆነው ቀሩ። ይኸው እስከ ዛሬ ድረስም እንጠቀምባቸዋለን። ይኸ ባይሆን ኖሮ የደብረ-ብርሃንና የደብረ-ሲናን ዋሻ መንገዶችን፣ የለማሊሞንና የአላማጣን ቁልቁለቶችና ዓቀበት ጠመዝማዛ መንገዶችን ማን ይሠራቸው ነበር?

የዘመናችን የምሁራን ደናቁርት ግን ይህ ዓይነቱ አርቆ ማየት ይቅርና ከገገርው ፓርቲ በያዙት ትርኪ-ምርኪና ዕለታዊ የፖለቲካ እንካስላንትያ ዓይናቸው ታውሮ፣ አንገብጋቢ የሃገር ጉዳይና ተራው ቁርቁስን ለይቶ ማየት ተስኗቸው፣ ደብዙም ጠፍቷቸው፣ ለባዕድ ኃይሎችና ለጠላት መንግሥታት መሣሪያ ሆነው፣ በእናት ሃገርና በወገናቸው ላይ የኢኮኖሚ ጫና እንዲደረግ መለመን ምን ዓይነቱ ወራዳነት ነው? አእምሯቸውንስ ምን አደነቆረው እንላለን። ተጎጂው ድኻው ወገናችው መሆኑንስ እንዴት ዘነጉት!

ከሓዲዎቹ በቅርቡ የጀመሩት እንቅስቃሴም አለ። ይኸም የኢትዮጵያ አየር መንገድ ወደ ካናዳ ሊከፍት ያቀደውን አዲስ መስመር ለማሰናከል መነሳታቸው ነው።

**በዚህም ኢትዮጵያዊ ሁሉ እንዲቃወማቸው፣ በሚያደርጉትም ሥራ ትብብር እንዳይሰጣቸው ለሁሉም ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ኣደራ እንላለን።**

**ገ/ኢ. ጐርፉ።**

**ማስታወሻ፦**

1. የነጋድራስ ኣፈ-ቄሳር ታሪክ የተገኘው ባሕሩ ዘውዴ በጻፈው Pioneers of Change in Ethiopia ከተባለው መጽሓፍ ነው።
2. የራስ ሙሉጌታ ታሪክና ፎቶግራፍ ደግሞ ኣሌኻንድሮ ዴልባዩ ጽፎት ተስፋዬ መኰነን ባይለየኝ ከተረጎመው “ቀይ ኣንበሳ” ከተባለው መጽሓፍ ተገኘ።